# የዕብራውያን መጽሐፍ

## ትምህርት አንድ

# የዕብራውያን መጽሐፍ ዳራና ዓላማ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ  አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**

ሀ. ጸሐፊ

1. መለያ
2. ገፅታ/ የግለታሪክ ገፅታ

ለ. ቀደምት ተደራሲያን

1. አይሁድ
2. ሔለኒስቶች
3. ያልበሰሉ
4. በስደት ላይ ያሉ
5. ወደ ክህደት እየተንደረደሩ ያሉ

3. **ዓላማ**

ሀ. የምክሩ ቃል ጥብቅነት

1. ድግግሞሽ
2. አሳማኝ ቅርፅ

ለ. የምክሩ ቃል ግብ

1. በአካባቢው ያለውን ትምህርት መቃወም
2. ለኢየሱስ ታማኝ ሆኖ መዝለቅ

4. **ማጠቃለያ**

# የዕብራውያን መጽሐፍ

## ትምህርት አንድ

## የዕብራውያን መጽሐፍ ዳራና ዓላማ

# መግቢያ

በየታሪክ ዘመናቱ ሁሉ የክርስቶስ ተከታዮች በብዙ ስደትና መከራ ውስጥ ያልፉሉ፡፡ የንብረት መዘረፍ፣ ድብደባ፣ እስር እና መሰዋት ቁጥር ስፍር የሌላቸው ክርስቲያኖች ዕጣፈንታ ነበር፡፡ አንዳንድ ዘገባዎች እንደሚያሳዩንም፣ በእኛም ዘመን ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ክርስቲያኖች መከራና ስደት እየተቀበሉ ነው፡፡

ይህንን የመሰለ ስደት አይተን ለማናውቅ ግን፣ ስደትና መከራ ስለሚያስከትለው ፈታኝ ነገር መገመት አዳጋች ነው፡፡ በሰላምና ከስጋት ነፃ በሆነ መንገድ የሚኖሩ ክርስቲያኖች አብዛኛውን ጊዜ ምንም ፈተና ሳይኖርባቸው እምነታቸውን ሲያመቻምቹ ይታያሉ፡፡ ራስን፣ የትዳር ጓደኛን፣ ልጆችን፣ እና የቅርብ ጓደኞችን ከጉዳት ለማዳን ሲባል እምነትን ለድርድር ማቅረብ ምን ያህል እንደሚፈታተን ይታያችኋል? ታዲያ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ክርስቲያኖችን እንዴት ማበረታታት ይቻላል?

የዕብራውያንን መጽሐፍ ጸሐፊ የተጋረጠበት ተግዳሮትም ይኸው ነበር፡፡ ባለፉት ዘመናት በመከራና በስደት ውስጥ ላለፉና አሁን ደግሞ በባሰ ፈተና ውስጥ እያለፉ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ነበር የጻፈው፡፡ በላፉት ዓመታት በድል አልፈዋል፣ አሁን ግን ከበለጠ መከራና ስደት ራሳቸውን ለማዳን ሲሉ ከክርስቶስ ዘወር እንዳይሉ የዕብራውያን ጸሐፊ ሰግቷል፡፡

*የዕብራውያን መጽሐፍ* ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርት ይህ የመጀመሪያው ትምህርት ሲሆን "የዕብራውያን መጽሐፍ ዳራና ዓላማ" የተሰኘ ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርታችን፣ የዚህን ውስብስብ መጽሐፍ አፈታት አቅጣጫ የሚያስይዙልንን በርካታ አመለካከቶች እናስተዋውቃለን፡፡

ርዕሳችን እንደሚያመለክተው፣ የዕብራውያንን መጽሐፍ ዳራና ዓላማ በሁለት መንገዶች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የመጽሐፉን ዳራ እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ዕብራውያን እንዲፃፍ ምክንያት የሆነበትን ገዢ ዓላማ ጠቅለል አድርገን እናያለን፡፡ እስኪ ከዕብራውያን መጽሐፍ ወሳኝ ዳራ ጋር ተዛማጅ የሆኑትን ጉዳዮች በመዳሰስ እንጀምር፡፡

# ዳራ

እርስ በርሳቸው ተዛምዶ ያላቸውን ሦስት ርዕሶች በመዳሰስ የዕብራውያንን ዳራ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ ጸሐፊውን እንመለከታለን፡፡ ከዚያም ቀደምት ተደራሲያኑን እንመረምራለን፡፡ በመጨረሻም፣ የዕብራውያን መጽሐፍ የተፃፈበትን ቀን እናያለን፡፡ እስኪ አስቀድመን የዕብራውያንን ጸሐፊ እንመልከት፡፡

# ጸሐፊ

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ማንነትን አስመልክቶ የተለያዩ አቋሞች ይንፀባረቁ ነበር፡፡ ለእኛ ዓላማ ግን፣ ሁለት ጉዳዮችን ብቻ እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የጸሐፊውን ማንነት እናነሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በመጽሐፉ ውስጥ የሚታዩ ገፅታዎችን በመመርመር የጸሐፊውን ግለ ታሪካዊ ገፅታ እናመለከታለን፡፡ አስቀድመን የጸሐፊውን ማንነት በመመርመር እንጀምር፡፡

## ማንነት

የዕብራውያንን መጽሐፍ ጸሐፊ ማንነት የመለየቱ ጉዳይ እንደሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቀላል አይሆንም፣ ምክንያቱም ጸሐፊው ስለማንነቱ ምንም ፍንጭ አልሰጠምና ነው፡፡ ከጥንት አባቶች ዘመን አንስቶ፣ ማለትም በግምት ከ150 እስከ 215 ዓ.ም. የኖረው የአሌክሳንድርያው ክሌመንት እና ከ185 እስከ 254 ዓ.ም. የኖረው የአሌክሳንድርያው ኦሪገን እንደገለጡት በእነርሱ ዘመን የዕብራውያንን መጽሐፍ ማን ጻፈው? ለሚለው ጉዳይ በርካታ ሃሳቦች ይሰነዘራሉ፡፡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ፣ በተደጋጋሚ ጊዜ ለጸሐፊነት የሚታጨው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው፣ ምሁራን ግን፣ በርናባስ፣ ሉቃስ፣ አጵሎስ እና የሮማው ክሌመንት ጽፈውታል የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡

በ325 ዓ.ም. አካባቢ የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የነበረው ኢዮሲቢስ *History of the Church* በስድስተኛው መጽሐፍ፣ ምዕራፍ 25 ክፍል 14 ውስጥ ስለ ዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ የኦሪገንን አመለካከት ጠቅሶ ከታች የምናነብበውን ጽፏል፡

> **የዕብራውያንን መልእክት ማን ጻፈው? ስለሚለው ጉዳይ እውነቱን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡**

ኦሪገን የሰጠው ሃሳብ የሚያሳየን በእርሱ ዘመን የነበሩ ሰዎች ይሰማቸው እንደነበረ ሁሉ እርሱም በጉዳዩ እርግጠኛ እንዳልነበረ ያንጸባርቃል፡፡ በእኛም ዘመን ያሉ ምሁራንም በዚህ ሃሳብይስማማሉ፡፡ ይህንን መጽሐፍ ማን እንደጻፈው በእርግጠኝነት የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

ስለ ዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ማንነት የሚነሱ ጥያቄዎች እና አንዳንድ የሐሰት መምህራኖች የዕብራውያንን መጽሐፍ በተጣመመ መንገድ የመጠቀማቸው ጉዳይ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መካተት ይገባዋል የሚለውን ጉዳይ በጥንት አባቶች ዘመን ከነበሩት እንዳንዶቹን እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል፡፡ እርግጥ ነው፣ በ99 ዓ.ም. አካባቢ የሞተውን፣ የሮማውን ክሌመንትን የመሳሰሉ እውቅ ምሁራን፣ ዕብራውያንን ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እኩል ስፍራ ሰጥተውታል፡፡ ከ100 እስከ 165 ዓ.ም. የኖረው ሰማዕቱ ጀስቲንም ተመሳሳዩን አድርጓል፡፡ ሆኖም የዕብራውያን መጽሐፍ በ144 ዓ.ም. በተፃፈው የማክሮናይት ቅጂም ሆነ፣ በ170 ዓ.ም. በተፃፈው የሙራቶሪያን ቅጂ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ሆኖም፣ በጥንት አባቶች ዘመን ማብቂያ አካባቢ፣ በምዕራቡና በምሥራቁ ዓለም የሚገኙ ዕውቅ ተርጓሚዎች ዕብራውያንን የካኖኑ ክፍል አድርገው ተቀብለውታል፡፡ ሁላቸውም በጥቅሉ ጸሐፊው ጳውሎስ በመሆኑ ላይ ተስማምተዋል፡፡

በመካከለኛው ዘመን ይኖሩ ከነበሩ እውቅ ምሁራን አብዛኞቹ፣ ዕብራውያንን ጳውሎስ ጽፎታል በሚለው እምነታቸው ገፉበት፡፡ በተሃድሶ ዘመን ግን፣ የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አራማጆች የጳውሎስን ጸሐፊነት ጨምሮ፣ አብዛኞቹን ትውፊታዊ የቤተክርስቲያን ታሪኮች ጥያቄ ውስጥ አስገቡ፡፡ ማርቲን ሉተር ጸሐፊው አጵሎስ ነው የሚል ሃሳብ አቀረበ፡፡ ጆን ካልቪን ደግሞ አማራጭ አልሰጠም፣ ሆኖም መጽሐፉ ከጳውሎስ አልተገኘም በማለት ተሟገተ፡፡

ዛሬ፣ አብዛኞቹ ተርጓሚዎች የጳውሎስን ጸሐፊነት ውድቅ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ አቋም፣ ሦስት ምክንያቶችን እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ አስቀድመን እንደጠቀስነው፣ ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ ስሙን የመጥቀስ ልምምድ ነበረው፣ ይህ መጽሐፍ ግን የጸሐፊውን ማንነት አይጠቅስም፡፡ እንዲያውም፣ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡2 በግልፅ እንደሚያስቀምጠው፣ አስመሳዮች በስሙ በርካታ ጽሑፎችን እያሰራጩ መሆናቸው በጣም እንዳሳሰበው ጠቅሷል፡፡ በዚህ ወቅት የዕብራውያንን መጽሐፍ እንደጻፈ አለመጥቀሱ በፍፁም ያልተለመደ ነው፡፡

ሁለተኛ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው ነገሮች ጋር እምብዛም ተመጋጋቢነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ አትኩሮት አድርጓል፡፡ ለምሳሌ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ መልከጼዴቅን ሦስት ጊዜ ጠቅሷል፡፡ በብሉይ ኪዳኑ የመገናኛው ድንኳን ላይ ትኩረት እንዲደረግ አድርጓል፡፡ ክርስቶስንም እንደ ሊቀ ካህን በስፋት ገልፆታል፡፡ እነዚህን ሁሉ በአንድነት በመውሰድ፣ እነዚህ መሪ ሃሳቦች የዕብራውያን መጽሐፍ ከተቀሩትና በጳውሎስ መጻፋቸውን ከምናውቃቸው መሕፍት የተለየ ያደርጉታል፡፡

ሦስተኛ፣ የጳውሎስን ጸሐፊነት እንድንጠራጠር የሚያደርገን ሌላው ጠንካራ ምክንያት የዕብራውያን ጸሐፊ ራሱን ከኢየሱስ ተከታዮች በጣም የማራቁ ጉዳይ ነው፡፡ በዕብራውያን 2፡3 የተጻፈውን አድምጡ፡

> ***ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት፥ (ዕብ 2፡3)***

በዚህ ስፍራ የዕብራውያን ጸሐፊ ድነት “አስቀድሞ በጌታ እንደተነገረ”፣ በሌላ አባባል፣ በኢየሱስ በራሱ እንደተነገረ ከዚያም “እርሱን በሰሙት ለእኛ እንደተረጋገጠ” ይጠቅሳል፡፡ ያም ማለት፣ ጸሐፊውና ተደራሲያኑ ከኢየሱስ በቀጥታ ከሰሙ ሰዎች የወንጌል መልእክት ተረጋግጦላቸዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው የክርስትና እምነቱን በሦስተኛ ወገንነት መቀበሉን ማመኑ በገላትያ 1፡1፣11 እና 12 ፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23 ጳውሎስ ወንጌልን በቀጥታ ከኢየሱስ ስለመቀበሉ ከሚያረጋግጥባቸው ክፍሎችጋር ይጣረሳሉ፡፡

> **“የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ማነው?” ለሚለው ጥያቄ አጭሩ መልስ፣ አናውቅም የሚለው ነው፡፡ ስለ ማንነቱ የሚናገሩ ጥቂት ፍንጮች ይኖሩናል፡፡ በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመናት ሁሉ ለዚያ ጥያቄ በርካታ ምላሾች ተሰጥተዋል፡፡ ለበርካታ ዓመታት ቤተክርስቲያን ጳውሎስ ጽፎታል ብላ ስታስብ ኖራለች፡፡ እኔ እንደማስበው ግን ጳውሎስ የጻፈው አይመስለኝም ምክንያቱም በዕብራውያንና በጳውሎስ መልእክቶች መካከል ልዩነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በተደጋጋሚ ጊዜ ራሱን ከተደራሲያኑ ጋር የሚያስተሳስራቸውን ነገር ያነሳና ከዚያም የደብዳቤውን ነገረ-ጉዳይ ያነሳል፡፡ ዕብራውያን ግን እንዲህ አያደርግም፡፡ በዕብራውያን ውስጥ ክርስቶስን እንደ ታላቅ ሊቀካህን የሚገልጡ መሪ ሃሳቦች አሉ ያ ደግሞ በጳውሎስ ደብዳቤዎች ገፅታ ውስጥ በብዛት የምታገኙት አይደለም፡፡ ስለዚህ፣ ምናልባት ጸሐፊው ጳውሎስ ላይሆን**

**ይችላል፡፡ በርናባስ ወይም አጵሎስ ጵፎት ይሆናል የሚሉ ሃሳቦችም አሉ፡፡ ማርቲን ሉተር ደግሞ አጵሎስ ወይም ጵርስቅላ ሊሆኑ ይችላሉ ይላል፡፡ ይህም ሁሉ ሆኖ፣ በእርግጥ አናውቀውም፡፡ በተሻለ መንገድ ማለት የምንችለው የዕብራውያን ጸሐፊ የሁለተኛው ትውልድ አማኝ ነው የሚለውን ይሆናል፡፡ በምዕራፍ 2 እንደሚናገረው ከክርስቶስ ስለሰሙት ይናገርና እነርሱም የሰሙትን እንዳስተላለፉ ይጠቅሳል፣ እናም ራሱን በሁለተኛው ትውልድ ውስጥ የሚያስቀምጥ ይመስላል፡፡**

**ዶ/ር ስቴፋን ኢ. ዊትመር**

*የዕብራውያንን ጸሐፊ ማንነት መርምረናል ደግሞም ማንነቱ ያልታወቀ ሆኖ መዝለቁንም አይተናል፡፡ ሆኖም ስለ ጸሐፊው ግለ ታሪካዊ ገፅታ አንድ ነገር ማመልከት እንችላለን፡፡*

## ግለ ታሪካዊ ገፅታ

ከጊዜ አንፃር፣ ስለ ፀሐፊው ሕይወት በግልፅ የተቀመጡ ሁለት ገፅታዎችን እናመለክታለን፡፡

***ሄለኒስት አይሁድ፡፡*** በመጀመሪያ ደረጃ የዕብራውያን ጸሐፊ ሄለኒስት አይሁድ ነው፡፡ በእኛ ዘመን የሚገኙ አብዛኞቹ ምሁራን ጳውሎስ ዕብራውያንን አልጻፈም ይላሉ፡፡ ስለዚህ በእውነት የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው ከሚለው የኦሪን ድምዳሜ ጋር መስማማት ይሻላል፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊነት ለበርካታ ዓመታት አከራካሪ ሆኖ ዘልቋል፣ ሆኖም ይህ ድምዳሜ በምንባቡ ውስጥ ከምናገኛቸው ፍንጮች ስለ ጸሐፊውና ስለ ባህርዩ ለመረዳት የተቻለንን ያህል እንዳንጥር ሊገታን አይገባም፡፡

ከምንባቡ እንደምንመለከተው አይሁድም ሆኑ ሄለኒስቶቹ (ግሪኮቹ) በጸሐፊው እና በመጽሐፉ ላይ ተፅእኖ አሳድረዋል፡፡ የጸሐፊው ጠንካራ አይሁዳዊ ዝርያ በብሉይ ኪዳን እውቀቱ ውስጥ በግልፅ ይታያል፡፡ እንዲያውም፣ በ13 ምዕራፎች ውስጥ ቢያንስ 31 ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ጠቅሷል፡፡

በተጨማሪም ጸሐፊው ጠንካራ ግሪካዊ (ሄለኒስት) አስተዳደግ ያለው መሆኑም ይታያል፡፡ ቀደም ባለው ዘመን፣ ጸሐፊው ሰብዓሊቃናት ማለትም የብሉይ ኪዳን ግሪክኛ ቅጂን መጠቀሙን ሄለኒስት አይሁድ የመሆኑ ማስረጃ አድርገው ተርጓሚዎች ያመለክቱ ነበር፡፡ ካለፈው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በኋላ ግን፣ በሙት ባህር የተገኘው ጥቅልል እንዳመለከተው ከሰፕቱዋጀንት በቀጥታ ተወስደዋል ተብለው ይታሰቡ የነበሩ ጥቅሶች ከሌሎች የዕብራይስጥ ትውፊታዊ ምንባቦች ተወስደው ሊሆን ይችላል በማለት አመልክቷል፡፡ በዚህ ምክንያት፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ሰብዓሊቃናትን ስለመጠቀሙ እርግጠኛ ልንሆን አንችልም፡፡

ይህ ግኝት እንዳለ ሆኖ፣ ጸሐፊው  ሄለኒስት ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ የተራቀቀ የግሪክኛ አጣጣሉ የግሪካዊ አስተዳደግ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የቃላት አጠቃቀሙና ዘይቤው ከሉቃስ ጽሑፎችም ይልቅ ምጡቅ መሆኑን ከቋንቋው ልዕቀት እንገነዘባለን፡፡

***ጥልቅ ስሜት ያለው ምሁር፡፡*** የዕብራውያን ጸሐፊ ሄለኒስት አይሁድ ብቻ ሳይሆን፣ ጥልቅ ስሜት ያለው ምሁር መሆኑንም በግለ ታሪካችን ውስጥ ልናክል ይገባናል፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ ምሁር የመሆኑን ጉዳይ ተርጓሚዎች በስፋት እውቅና ይሰጡታል፡፡ በዕብራውያን ውስጥ የሚነሱ ነገረ-መለኮታዊ ሙግቶች በተቀሩት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከምናገኘው በበለጠ ውስብስብ ነው፡፡

እንዲያውም፣ ጸሐፊው ራሱ ዕብራውያን 5፡13-14 በመሳሰሉት ክፍሎች ውስጥ እንደሚያመለክተው መልካሙን ከክፉው ለመለየት፣ የክርስቶስ ተከታዮች በአስተምህሮ በሳል ሊሆኑ ስለሚገባ የተራቀቁ ነገረመለኮታዊ ትንታኔዎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ጠቅሷል፡፡

**ከዕብራውያን መልዕክት ይዘት እንደምንረዳው፣ ስለ ጸሐፊው ልንናገር የምንችላቸው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ከነዚያም መካከል አንዱ ብሩኅ አዕምሮ ያለው መሆኑ ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ግሪክኛ ቅጂ የሆነውን ሰብዓ ሊቃናት ወደፊትም ወደኋላም ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ተውፊታዊ የሆነውን አይሁዳዊ ተደራሲ አሳማኝ በሆነ መንገድ ምንባቦችን እንዴት እንደሚያቀርባቸው በትክክል ይገነዘባል፡፡ ምናልባትም ለሄለኒስት አይሁድ ተደራሲያን የጻፈ ሄለኒስት አይሁድ ጸሐፊ ሊሆን ይችላል፡፡ "ሄለኒስት አይሁድ" ስል፣ ግሪክ ተናጋሪ የሆኑ ምናልባትም በየሀገሩ የተበተኑ (ዲያስፖራዎች) ሆነው፣ ከአይሁድ ትውፊታቸው ረገድ ግን ራሳቸውን የሰጡ እና ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያውቁ ናቸው፡፡**

**ዶ/ር ግሬግ ኤስ. ኔር**

የዕብራውያን ጸሐፊ ምሁር መሆኑ እውቅና ሊሰጠው ቢገባም፣ ቀዝቃዛ፣ ፊደል የቆጠረ አዋቂ፣ ብቻ አልነበረም፡፡ ስለ ክርስትና እምነት ጥልቅ ስሜት ያለው ሰው ነው፡፡ ስለ ክርስቲያን ወገኖቹ ያለው መሰጠትና ጥልቅ ስሜት በጽሑፎቹ ውስጥ በግልፅ ይታያል፡፡

በዕብራውያን 10፡33-34 ከተደራሲያኑ ጋር የነበረውን ግልፅ ትስስር የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

***ነገር ግን ግማሽ በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ ስለ ሆናችሁ ግማሽም እንዲህ ካሉት ጋር ስለ ተካፈላችሁ፥ ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ መከራ በሆነበት በትልቅ ተጋድሎ የጸናችሁበትን የቀደመውን ዘመን አስቡ።***
***የሚበልጥና ለዘወትር የሚኖር ገንዘብ በሰማይ ራሳችሁ እንዳላችሁ አውቃችሁ፥ በእስራቴ ራራችሁልኝ የገንዘባችሁንም ንጥቂያ በደስታ ተቀበላችሁ።***

በተመሳሳይ መንገድ፣ በ12፡1-2 ውስጥ ስለ ክርስቶስ ያለውን ጥልቅ ስሜት እንዲህ ሲል ይጠቅሳል፡

***እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና። (ዕብ 12፡1-2)***

እነዚህን ተመሳሳይ ምንባቦች ጸሐፊው ከሰብዓዊ ግንኙነት ሩቅ ሊሆን እንደማይችል ሳይረዱ ማንበብ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለ ተደራሲያኑና ስለ ክርስቶስ ጥልቅ ስሜት ያለው ነበር፡፡ ይህንን ጥልቅ ስሜት ከሳትነው፣ የመጽሐፉን አንድ ወሳኝ ገፅታ እንስታለን፡፡

**ስለ ጸሐፊው የምንገነዘበው ተጨማሪ ነገር ስለሚሰብካቸውና ስለሚጽፍላቸው ሰዎች በእውነት ግድ ይለው የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ስለ መንፈሳዊ ግድየለሽነታቸው ግድ ይለው**

**ስለነበር፣ ስለ መድከምና ስለ ዝለት አልፎም ስለ ክህደት አደጋዎች አሁንም አሁንም ያሳስባቸዋል፡፡ ስለዚህም፣ እርሱ አሰደናቂ የነገረ-መለኮት ምሁር እና የቅዱሳት መጻሕፍት ተርጓሚ፣ ደግሞም ተደራሲያኑን አስተማማኝ በሆነ መንገድ በግሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር፡፡ ስለ እነርሱ በእውነት ግድ ስለሚለው፣ ከነገረመለኮት፣ ከቅዱሳት መጻሕፈት አፈታት እና በመንፈሳዊ ጉዟቸው ከማዛመድ አንፃር ሁሉን ጠንቅቆ ለማስረዳት ከፊታቸው የሚቀድም አዝማቻቸው ነበር፡፡**

**ዶ/ር ኤካርድ ሽናቤል**

የዕብራውያንን መጽሐፍ ዳራ አስመልክቶ እስካሁን ባደረግነው ጥናት በመጽሐፉ ጸሐፊ ማንነት ላይ አተኩረናል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ሁለተኛው ጉዳያችን መሸጋገር ይገባናል፡፡ እርሱም የዕብራውያን መጽሐፍ ቀደምት ተደራሲያን የሚለው ነው፡፡

# ቀደምት ተደራሲያን

የዕብራውያን መጽሐፍ የተደራሲያኑን ማንነት በስም፣ በከተማ ወይም በክልል በግልፅ አያስቀምጥም፡፡ ሆኖም፣ በጥቅል አገላለጽ፣ ጸሐፊው ራሱ በግል ለሚያውቃቸው ግልፅ ተደራሲያን የጻፈ መሆኑን በልበ ሙሉነት መናገር እንችላለን፡፡ በ13፡19-24 ውስጥ በድጋሚ ሊያያቸው የሚፈልግ መሆኑን ለተደራሲያኑ ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ስለ ጢሞቴዎስም፣ “ወንድማችን” በማለት የሚናገር ሲሆን፣ ከኢጣሊያ ስለሆኑትና ተደራሲያኑ በግልፅ ስለሚያውቋቸው ቡድኖች ይጠቅሳል፡፡

የዕብራውያንን መጽሐፍ በምናጠናበት ወቅት ስለ እነዚህ ቀደምት ተደራሲያን ልብ ልንል የሚገቡንን አምስት ወሳኝ ጉዳዮች እንመለከታለን፡፡

## አይሁድ

በመጀመሪያ፣ ቀደምት ተደራሲያኑ አይሁድ ናቸው ብለን እንድናስብ የሚያስችለን ቢያንስ አንድ ጥሩ ክፍል እናገኛለን፡፡ ዕብራውያን 1፡1 ይህንን ግልፅ ያደርግልናል፡

> ***ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ (ዕብራውያን 1፡1)***

በዚህ ስፍራ፣ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ራሱን ለእስራኤል እንዴት እንደገለፀ ጸሐፊው ይጠቅሳል፡፡ ግን የብሉይ ኪዳኖቹን እስራኤላውያን “አባቶቻችን” በማለት የጸሐፊውና የተደራሲያኑ ዝርያዎች መሆናቸውን እንዴት እንዳመለከተ ልብ በሉ፡፡

ከ155 እስከ 230 ዓ.ም. ድረስ ከኖረው ከተርቱልያን ዘመን አንስቶ መጽሐፉ “ወደ ዕብራውያን” *“Pros Hebraious,”* የሚል ትውፊታዊ መጠሪያ እንዲኖረው መደረጉ አያስደንቅም፡፡

## ሄለኒስቶች

ሁለተኛ፣ የተደራሲያኑ አብዛኛው ክፍል ሄለኒስቶች ይመስላሉ፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ይዘት በፓለስታይን ውስጥ ከሚኖሩና ተውፊታዊውን መንገድ ከሚከተሉት ይልቅ ከፓለስታይን ውጪ

በሚኖሩ አይሁዳውያን መካከል የተለመደ የነበረውን ነገረ-መለኮታዊ አስተምህሮ ጠንቅቀው የሚያውቁ አይሁድ ተደራሲያንን ያነጣጠረ እንደሆነ ያመለክተናል፡፡

አብዛኞቹ ተርጓሚዎች ተደራሲያኑ ከፓለታይን ውጪ የት ይኖሩ እንደነበር ለመለየት ሙከራ አድርገዋል፡፡ በ95 ዓ.ም. አካባቢ መጽሐፉን በማጣቀስ የጻፈው የሮሙ ክሌመንት የመጀመሪያ ደብዳቤ ተደሲያኑ በሮም ይኖሩ ነበር የሚል ድምዳሜ ላይ አንዳንዶቹን አድርሷቸዋል፡፡ ለዚህም ድምዳሜ የሚጠቀሰው አጋዥ ክፍል በዕብራውያን 13፡24 ያለውና "ከኢጣሊያ የሆኑቱ" በማለት የተጠቀሰው ነው፡፡እነዚህ ሃሳቦች ማራኪ ናቸው፣ ሆኖም በየትኛውም ደረጃ በእርግጠንነት፣ መናገር የምንችለው፣ ቀደምት ተደራሲያኑ ከፓለስታይን ውጪ ይኖሩ የነበሩ ሄለኒስቶች (ግሪክኛ ተናጋሪ አይሁድ) ነበሩ የሚለውን ብቻ ነው፡፡

**ያልበሰሉ**

ሦስተኛ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ቀደምት ተደራሲያን ያልበሰሉ የነበሩ መሆናቸው ነው፡፡ ዕብራውያን 5፡12 ጸሐፊው እንዴት እንደገለጣቸው አድምጡ፡

> ***ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። (ዕብራውያን 5፡12)***

ጸሐፊው "ከጊዜው የተነሳ (በአሁኑ ወቅት) አስተማሪ ልትሆኑ ሲገባችሁ" የሚለውን ሲጠቅስ ተደራሲያኑ ካመኑ ረጅም ዘመናት ያሳለፉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ትልቅ አስተምህሮታዊ እድገት ሊያሳዩ ይገባቸው ነበር፡፡ ሆኖም ጸሐፊው እንደጠቀሰው፣ "ገና የእግዚአብሔርን ቃል እውነት መሠረታዊ ትምህርቶች" የሚያስተምራቸው ይፈልጋሉ፡፡

በሚያስገርም ሁኔታ ግን፣ ተደራሲያኑ ነገረ-መለኮታዊ ብስለት የጎደላቸው ቢሆኑም፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ግን በጠቅላላው አዲስ ኪዳን ከሚገኙት ይልቅ ምጡቅና ውስብስብ ነገረመለኮታዊ አስተምህሮዎችን ይዟል፡፡ ታዲያ እነዚህ የመጽሐፉ ገጽታዎች ካልበሰሉት ተደራሲያኑ ጋር እንዴት ይጣጣማሉ? ይህንን ሁኔታ ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ልንረዳው የምንችለው የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ምኩራቦች የነበረውን የተለመደ ልምምድ የራሳቸው ያደረጉ መሆኑን በልቡና በማስቀመጥ ነው፡፡

ከሉቃስ 4፡16፤ የሐዋርያት *ሥራ* 13፡15 እና 1ኛጢሞ 4፡13 እንደምንረዳው፣ የምኩራቡ መሪዎች እና የክርስቲያኖቹ ቤተክርስቲያናት በየማኅበረ ምዕመናቸው የእግዚአብሔርን ቃል ንባብና ማብራሪያ አሰጣጥ ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ የዕብራውያን ጸሐፊ እጅግ ውስብስብ የሆኑ ነገረ-መለኮታዊ የአዲስ ኪዳን ቋንቋዎችን የተጠቀመው የቤተክርስቲያን መሪዎች መጽሐፉን ለህዝባቸው ያስተምራሉ ብሎ ስለሚጠብቅ ነው፡፡ በዕብራውያን 5፡11፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ተደራሲያኑን ለመማር የዘገዩ መሆኑን በመጥቀስ ገስጾአቸዋል፡፡ ስለዚህም አብዛኞቹ ቀደምት ተደራሲያኑ ለመሪዎቻቸው አክብሮት ስለሌላቸው በነገረ-መለኮቱ ረገድ ያልበሰሉ ሆነው መዝለቃቸውን ማሰብ ይቻላል፡፡

ይህ ሃሳብ በዕብራውያን 13፡17 ተረጋግጧል፡፡ በዚያም ጸሐፊው ተደራሲያኑን እንዲህ ይላቸዋል፡

> **ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ። (ዕብራውያን 13፡17)**

## መከራን የተቀበሉ

አራተኛ፣ የዕብራውያን ቀደምት ተደራሲያን መከራን የተቀበሉ ነበሩ፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የነበሩ ክርስቲያኖች የተቀበሉዋቸው ሁለት የታወቁ የመከራ ወቅቶች ነበሩ፡፡ ይህም በዕብራውያን መጽሐፍ ተደራሲያን ላይ በተዘዋዋሪም ቢሆን ተፅዕኖ አሳድሮባቸው ነበር፡፡ በ49 ዓ.ም.፣ ንጉሥ ክላውዴዎስ አይሁዳውያንን ከሮም አባርሮ ነበር፡፡ በ64 ዓ.ም. ደግሞ፣ ንጉሥ ኔሮ በሮም አቅራቢያ የሚገኙ ክርስቲያኖችን ያሳድድ ነበር፡፡

የዕብራውያንን መጽሐፍ ስናነብብ፣ የዕብራውያን ቀደምት ተደራሲያን አስቀድሞውኑ በስደት ውስጥ ያለፁ መሆናቸው ግልፅ ይሆንላችኋል፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ በዚያን ወቅት መከራን እየተቀበሉ ነበሩ፡፡ እናም አብዛኞቹ በመከራ ውስጥ እያለፉ እንደሆነና እንዲያውም ወደፊት የከፋ መከራ እንደሚጠብቃቸው ጸሐፊው የሚጠብቅ መሆኑን እናያለን፡፡

በ10፡32-35፣ ከተደራሲያኑ ጥቂቶቹ አስቀድሞውኑ ስተቀበሉት መከራ ጸሐፊው ያመለክታል፡

> ***ነገር ግን ግማሽ በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ ስለ ሆናችሁ ግማሽም እንዲህ ካሉት ጋር ስለ ተካፈላችሁ፥ ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ መከራ በሆነበት በትልቅ ተጋድሎ የጸናችሁበትን የቀደመውን ዘመን አስቡ። ...እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ።***

በዚህ ስፍራ ጸሐፊው "ለመጀመሪያ ጊዜ ብርሃን ከበራላቸው በኋላ ባለፉበት መከራ" ስላሳዩት ጽናት ያመሰግናቸዋል፡፡ ደግሞም "ድፍረታቸውንም እንዳይጥሉ ያበረታታቸዋል"፡፡ በዚህ ስፍራ "ድፍረት" ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል *parrēsia* ሲሆን፣ በበርካታ አውዶች በባለሥልጣናት ፊት "ወኔ፣" አለማጣት "አለማፈግፈግ"፣ ወይም "አለመፍራት" የሚል ፍቺ ይይዛል፡፡ ይህ ግማሽ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተደራሲያኑ በአንድ መንገድ ይፋ የሆነ የአደባባይ መከራ የደረሰባቸውና ይህም ድፍረታቸውን እንዲጥሉ የተገዳደራቸው እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ጸሐፊው በ13፡3 ውስጥ በቀጥታ በወቅቱ ስለነበሩበት መከራ እንዲህ ይተቅሳል፡

> ***ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፥ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ። (ዕብ 13፡3)***

ጸሐፊው በዚህ ስፍራ "ከእነርሱ ጋር እንደታሰሩ ሆነው የታሰሩትን እንዲያስቡ" እና የተጨነቁትን ደግሞ ልክ "እራሳቸው በጭንቅ ውስጥ እንዳሉ አድርገው እንዲያስቡ" ተደራሲያኑን ያሳስባል፡፡ ተደራሲያኑ በጠቅላላ ባለፈው ጊዜ መከራን የተቀበሉ አለመሆናቸውን ይህ ጥቅስ ግልፅ ያደርግልናል፡፡

ቀድሞውኑ እና አሁንም መከራ ከመቀበላቸው ባሻገር፣ ተደራሲያኑ ገና ወደፊትም የበለጠ መከራ እንደሚቀበሉ በ12፡3-4 ውስጥ ጸሐፊው በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ እስኪ ማሰሰቢያውን አድምጡ፡፡

*በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፥ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ።*
*ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም፤*
*(ዕብ 12፡3-4)*

ይህ ምንባብ እንደሚያመለክተው፣ በተደራሲያኑ ላይ የበለጠ መከራ ይመጣባቸል ብሎ ጸሐፊው ይጠብቃል፣ እናም ስላሉበት ስለዚህ ሁኔታ በብርቱ ያስብ ነበር፡፡

> **የዕብራውያን መጽሐፍ ቀደምት ተደራሲያን ከበርካታ ጉዳዮች ጋር እየተጋፈጡ ነበር፡፡ ጸሐፊው በምዕራፍ 10 እንዳመለከተው፣ የተለያየ መከራ ደርሶባቸው ነበር፡ ጥቂቶቹ ንብረታቸውን ተዘርፈዋል፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ታስረዋል፣ በአንዳንድ ሁኔታ ደግሞ የአደባባይ ነቀፋ ደርሶባቸዋል፡፡ አሁንም ግን፣ መልእክቱን በሚጽፍበት ጊዜ፣ በክርስቶስ የደረሰውን ዘለፋ ለመቀበልና ከማኅበረሰቡም ለመገለል ፈቃደኛ እንዲሆኑ ያሳስባቸዋል፡፡ ይህንንም ለመግለጥ የተጠቀመው የብሉይ ኪዳኑን ቃል ሲሆን ያም ማለት ከምኩራቦቻቸው መገለል ሊሆን ይችላል፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄዱ ወቅት ደግሞ ከመቅደሱ የተገለሉ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ይህም ነገር እኔ እንደማምነው በሚጽፍበትም ወቅት ያለ ነገር ነበር፡፡ ስለዚህ ይጋፈጧቸው የነበሩ መከራዎች ይህንን ይመስሉ ነበር፡፡ በምዕራፍ 12 እንደሚናገረው ግን ይህ መከራ ደምን እስከማፍሰስ ገና አልደረሰም፣ ሆኖም በክርስቶስ በተገኘው ድል ከሞት ፍርሃት ነፃ የወጡ ስለ መሆናቸው እርግጠኛ ሊሆኑ እንደሚገባ ያሳስባቸዋል፡፡ ስለዚህ የምንረዳው ገና በጣም ብርቱና፣ የከፋ መከራና ስደት ከአድማሱ ባሻገር ይጠብቃቸዋል ማለት ነው፡፡** (ዶ/ር ዴኒስ ኢ. ጆንሰን)

## ወደ ክህደት እየተንደረደሩ ያሉ

አምስተኛ፣ ዕብራውያን ተደራሲያኑ በመከራ ውስጥ ሲያልፉ፣ ቢያንስ ጥቂቶቹ ወደ ክህደት እየተንደረደሩ ነበር፡፡ በመከራዎቹ ምክንያት ከመድከምና ተስፋ ከመቁረጥ ባሻገር፣ እስከ ዘለቄታው ከክርስቶስ ኢየሱስ ፊታቸውን በማዞር አደጋ ውስጥ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 10፡26-27 ይህንን ማስጠንቀቂያ እናነብባለን፡

*የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥*
*የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።*
*(ዕብ 10፡26-27)*

በዚህ ስፍራ ግን የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ጥቃቅን ስህተቶች ወይም ኃጢአቶች እየጠቀሰ እንዳልሆነ ግልጥ ሊሆንልን ይገባል፡፡ ተደራሲያኑን በብርቱ የሚያስጠነቅቀው እስከ ዘለቄታው ከክርስቶስ ለሚመለሱ ሰዎች፣ "የኃጢአት መስዋእት አይቀርልንምና" በማለት ነው፡፡ ሰዎች የክርስትናን እምነት ከተቃወሙ፣ ማለትም ከዕብራውያን ቀደምት ተደራሲያን ጥቂቶቹ እንደተፈተኑ ሁሉ፣

አሁንም ያንን የሚያደርጉ ለድነት የሚያበቃው እምነት የሌላቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ለእግዚአብሔር ጠላቶች የተጠበቀውን "ሊበላ ያለውን እሳትና የሚያስፈራ ፍርድ ይጠባበቃሉ"፡፡

በሚቀጥለው ትምህርታችን እንደምናብራራው፣ ይህና ሌሎችም ተመሳሳይ ምንባቦች እውነተኛ አማኞች ድነታቸውን ያጣሉ የሚል መልእክት አልያዙም፡፡ ይልቁኑ፣ ይህ ጥቅስ የሚያጣቅሰው እናምናለን ብለው እየተናገሩና በርካታ በረከቶቹንም እየተካፈሉ፣ ዳግም ያልተወለዱትንና ጽድቅን በእምነት ያልተቀበሉትን ነው፡፡ በሁሉም ሁኔታዎች፣ ከዕብራውያን ቀደምት ተደራሲያን መካከል አንዳንዶቹ እምነትን በመተው ፈተና ውስጥ የወደቁ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

የዕብራውያንን መጽሐፍ ዳራ የመጽሐፉን ጸሐፊ ማንነትና ቀደምት ተደራሲያኑን በመመርመር ከተመለከትን፣ ወደ ሦስተኛው ጉዳያችን መሸጋገር ይገባናል፣ ያም የዕብራውያን መጽሐፍ የተጻፈበት ጊዜ ነው፡፡

## ጊዜ

ዕብራውያን የተጻፈበት ትክክለኛ ቀን ያለመታወቁ እንደተጠበቀ ቢሆንም፣ የመጽሐፉን ቀደምትና የኋላ ቀናት በእርግጠኝነት መናገር ግን ይቻላል፡፡ አስቀድመን መጽሐፉ ተጽፏል ተብሎ የሚነገርበትን ቀደምት ጊዜ ወይም *terminus a quo* እንመልከት እና የኋለኛውን ወቅት ወይም *terminus ad quem* እንመልከት፡፡ እነዚህ ሁለቱም ቀናት በአስተማማኝነት ሊወሰኑ የሚችሉት የቅዱሳት መጻሕፍትንና ታሪካዊ መረጃዎችን በመጠቀም ነው፡፡

በአንድ በኩል፣ ዕብራውያን 13፡23 መጽሐፉ የተጻፈበትን ቀዳሚ ጊዜ እንድናረጋግጥ ይረዳናል፡፡ በዚህ ጥቅስ ጸሐፊው እንዲህ ጽፏል፡

> ***ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደ ተፈታ እወቁ፥ ቶሎ ብሎም ቢመጣ ከእርሱ ጋር አያችኋለሁ። (ዕብ 13፥23)***

በዚህ ስፍራ "ጢሞቴዎስ በቅርብ ከእስር እንደተፈታ" እንመለከታለን፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ጢሞቴዎስ መታሰር የሚናገር ሌላ ክፍል አናገኝም፡፡ እንዲያውም፣ ጳውሎስ ከመሞቱ ቀደም ብሎ በጻፈው፣ የ2ኛ ጢሞቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ ጢሞቴዎስ ነፃና ወዲያ ወዲህ በመጓጓዝ ለጳውሎስ ድጋፍ ያመጣለት ነበር፡፡ ይህ ጥቅስ እንደሚነግረን ግን፣ ዕብራውያን በተፃፈበት ወቅት ጢሞቴዎስ ታስሮ ከእስር ተፈትቶ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ሊጻፍ የሚችለው ከጳውሎስ ሞት በኋላ፣ በ65 ዓ.ም. አካባቢ ነበር ማለት ነው፡፡

በሌላ ጎን፣ መጽሀፉ ተጽፏል ተብሎ የሚገመትበት የመጨረሻው ወቅት 95 ዓ.ም. ሲሆን ይህም የሮሜው ክሌመንት በመጽሐፉ 1ኛ ክሌመንት የዕብራውያንን መጽሐፍ ጠቅሶ ከጻፈበት ጥቂት ቀደም ብሎ ነው፡፡

በተጨማሪ፣ አብዛኛዎቹ ተንታኞች እንደደረሱበት፣ ዕብራውያን 5፡1-3 በመሳሰሉት ምንባቦች፣ የሊቀ ካህኑን ከመስዋዕት ጋር የተያያዙ ተግባራት ለመግለፅ ጸሐፊው የተጠቀመው የአሁን ጊዜን ነው፡፡ ይህም እጅግ ወሳኝ ነው ምክንያቱም ጸሐፊው በተቀሩት የመጽሐፉ ክፍሎች ውስጥ ያለፉ ጊዜያትን ለማመልከት ይጠቀም የነበረው የግሪከኛውን የሃላፊ ጊዜ ነበር፡፡ እንግዲያው፣ ዕብራውያን በተጻፈበትም ወቅት የካህንነት ተግባራት እየተከናወኑ ነበር ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም፣ በ8፡13 ውስጥ እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ቃል ኪዳን ውስጥ ወደተቀመጡት ያረጁ የመስዋዕት ልምምዶች እንዳይመለሱ ጸሐፊው ተደራሲያኑን ያበረታታቸዋል፡፡ በአዲሱ ኪዳን መሠረት፣ እነዚያ ልምምዶች “ፈጥነው ይጠፋሉ፡፡” የሊቀ ካህንነት ተግባርና የሌዋውያኑ የመስዋዕት ሥርዓት በጠቅላላ ያበቃለት ሮማውያን ኢየሩሳሌምንና መቅደሷን ባወደሙበት በ70 ዓ.ም. እንደነበር እናውቃለን፡፡ ስለዚህ፣ ዕብራውያን የተጻፈበት ጊዜ በ65 ዓ.ም. ከጳውሎስ ሞት በኋላ እና በ70 ዓ.ም. ከመቅደሱ መፍረስ በፊት ይሆናል ማለት ነው፡፡

የዕብራውያንን ዳራና ዓላማ በምንዳስስበት ትምህርታችን ውስጥ እስካሁን የዕብራውያንን መጽሐፍ ዳራ የተለያዩ ገፅታዎች ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ የመጽሐፉን ዋና ሃሳብ ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ ዕብራውያን ለምን ተጻፈ?

# ዓላማ

እንደ ዕብራውያን መጽሐፍ ያለ ረጅምና ውስብስብ የትኛውም ዓይነት መጽሐፍ በልቡና ውስጥ ብዙ ዓላማ ሰንቆ እንደሚጻፍ መናገር ሚዛናዊነት ነው፡፡ ለእኛ ትምህርት ግን፣ የመጽሐፉን ገዢ ሃሳብ ጠቅለል አድርገን መመልከትን እናስቀድማለን፡፡ የዚህ መጽሐፍ ልዩ ልዩ ክፍሎች የየራሳቸው አጽንዖት አላቸው፣ እነዚህንም አፅንዖቶች በሚቀጥለው ትምህርታችን እንዳስሳለን፡፡ በዚህ ወቅት፣ መጽሐፉ በጠቅላላ በቀደምት ተደራሲያኑ ፅንሰ-ሃሳቦች፣ ባህርያትና ስሜቶች ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር እንዴት እንደተቀረፀ እናያለን፡፡

ተርጓሚዎች የዕብራውያንን መጽሐፍ ገዢ ዓላማ በተለያዩ መንገዶች ጠቅለል አድርገው አቅርበውታል፡፡ ለዚህ ጥናታችን ግን፣ የዕብራውያንን ቀደምት ዓላማ በዚህ መንገድ እንገልጠዋለን፡

> ***የዕብራውያን ጸሐፊ የጻፈው ተደራሲያኑ በአካባቢያቸው የተስፋፋውን የአይሁድ አስተምህሮ በመቃወም ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ለመምከር ነው፡፡***

ስለ ፀሐፊው የሰጠነው ይህ መግለጫ በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ለሚገኙት ዋና ሃሳቦች ታማኝ እንድንሆን ይረዳናል፡፡

እንደተናገርነው፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ተደራሲያኑን ለማሳሰብ ጽፏል፡፡ በ13፡22 ውስጥ ጸሐፊው ራሱ የተናገረበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***ወንድሞች ሆይ፥ የምክርን ቃል እንድትታገሡ እመክራችኋለሁ፥ በጥቂት ቃል ጽፌላችኋለሁና። (ዕብ 13፡22)***

በዚህ ስፍራ ጸሐፊው ተደራሲያኑ መጽሐፉን “እንደ ምክር ቃል” እንዲቀበሉት “እየመከረ” መሆኑን ልብ በሉ፡፡ እመክራችኋለሁ የሚለው ቃል *parakaleō* ከተሰኘው የግሪክ ግስ የወጣ ሲሆን፣ የግሪክኛው ስም ግሣዊ ቅርፁ ሲተረጎም ማሳሰቢያ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ይህ መምከር የተሰኘው ቃለ አገባብ የሚያሳየው “በተናጋሪው ሃሳብ ዙሪያ መሰባሰብን” ወይም “አንድ ሰው ከተናጋሪው

አመለካከት ጋር እንዲቆም መጥራትን” ይሆናል፡፡ ይኸው ተመሳሳይ መግለጫ መጥምቁ ዮሐንስ በሉቃስ 3፡18 ለንስሓ ያቀረበውን አጣዳፊና ሞጋች ጥሪ ለመግለጥም አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

በሚያስገርም መንገድ፣ “የምክር ቃል” የተሰኘው ሐረግ በሐሥ 13፡15 ውስጥ በጵስድያዋ አንፆኪያ ይገኙ የነበሩ የምኩራብ ሰዎች ጳውሎስና ባልደረቦቹ ቅዱሳት መጻሕፍትን ካነበቡላቸው በኋላ “ሕዝብን የሚመክር ቃል እንዳላችሁ” በማለት ሲጠይቋቸውም አልግሎት ላይ ውሏል፡፡ “ቃል” ወይም “የምክር መልእክት” የሚለው መግለጫ እኛ ዛሬ ስብከት ብለን የምንጠራው ቃል የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አቻ ስያሜ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

> **እንግዲህ ጸሐፊው በ13፡22 ውስጥ ሥራውን ከምክር ቃል ጋር አመሳስሎታል፡፡ ያም ማለት ዕብራውያን የምክር ቃል ነው ማለት ሲሆን፤ ያም መልእክት ማለት ነው፡፡ ሰዎችን ለማሳመን የሚደረግ ንግግር በመሠረታዊነት አልግሎት ላይ የሚውለው ተደራሲያኑ ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ጌታና አዳኛቸው መሆኑን በማመን ራሳቸውን በታማኝነት እንዲሰጡ ለማሳሰብ ነው፡፡ ስለዚህ፣ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ የቀረበው አሳማኝ ንግግር ወይም የዕብራውያን ድርሳን፣ የአይሁድን መጻሕፍት ለመተንተን መሪ ሃሳቦችን አስፋፍቶ ማቅረብ ይቻለው ዘንድ ለጸሐፊው ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ያም ማለት፣ የአይሁድን መጻሕፍት ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ለመተርጎም እና ጉልበታም በሆነ መንገድ ለማቅረብ፣ ተደራሲያኑም ጸሐፊው ምን አድርጉ እንደሚላቸው በትክክል እንዲረዱ ማድረግ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካኝነት ከሰጣቸው እና ክርስቶስ ከሰጣቸው ድነት ጋር በጽናት እንዲጣበቁ ይፈልጋል፡፡** (ዶ/ር ፍሬዴሪክ ሎንግ)

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ መልእክት ወይም ደብዳቤ ለተደራሲያኑ የምክር መልእክት ይዟል፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ግን ከየትኞቹም የአዲስ ኪዳን መልእክቶች በምክር ቃሎቹ ብርቱነት የተለየ ይሆናል፡፡

የጸሐፊውን ዓላማ ለመመርመር፣ ፣ በመጽሐፉ ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆኑትን የምክር ቃሎቹን ጥብቅነት በበለጠ ጥልቀት እንመልከት፡፡ ከዚያም ደግሞ፣ የእነዚህን ምክሮች ግብ በመመርመር፣ ጸሐፊው ከተደራሲያኑ የሚፈልገውን ምላሽ እንመልከት፡፡ በመጀመሪያ ጸሐፊው ለተደራሲያኑ ያቀረበውን ምክር ጥብቅነት እንመልከት፡፡

# የምክሩ ቃል ጥብቅነት

የጸሐፊው የምክር ቃል ጥብቅነት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በጥልቀት ለመመልከት ሁለት ጉዳዮችን እንዳስሳለን፡ በመጀመሪያ፣ በመጽሐፉ ውስጥ የምክር ቃሎቹን ድግግሞሽ፣ ሁለተኛ ደግሞ፣ ጸሐፊው ከምክር ቃሉ ጋር በተጓዳኝነት ያቀረበውን የማሳመኛ ንግግር ቅርፅ እንመለከታለን፡፡ የምክሩን ቃል ድግግሞሽ በመመልከት እንጀምር፡፡

## ድግግሞሽ

የጸሐፊው የምክር ቃል ድግግሞሽ የመልእክቱን አጣዳፊነት እንድንመለከት ያግዘናል፡፡ እነዚህ ምክሮች አንዳንድ ጊዜ ስውር ሲሆኑ፣ ቢያንስ 30 ጊዜ ያህል ግን በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ፣ ጸሐፊው የሚጠቀመው የግሪክ ሰዋሰው ምሁራን “hortatory subjunctive.”

ብለው የሚጠሩትን ነው፡፡ እነዚህ መለመንን ወይም መማፀን የተሰኙ ግሳዊ ቅርፆች የሚተረጎሙት “ይህንና ያንን እናድርግ” እየተባሉ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ4፡14፣16 ውስጥ ሁለት ምክሮችን እናብባለን፡

> *… ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ። … ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ። (ዕብ 4፡14፣16)*

ጸሐፊው በተጨማሪም ትዕዛዛዊ ቃሎችን፣ አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ብለን የምንተረጉማቸውን ቃሎች በመጠቀም ተደራሲያኑን ይመክራል፡፡ ለምሳሌ፣ በ12፡12-16 ይህንን መድበለ ምክር እናነብባለን፡

> *ስለዚህ የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ፤*
> *… ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ።*
> *ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ …*
> *የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረከሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፥ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፥*
> *ወይም ስለ አንድ መብል በኵርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ። (ዕብ 12፡12-16)*

ጸሐፊው ተደራሲያኑን በቀጥታ ደጋግሞ ምን ያህል እንደመከረ ልብ ማለት የሚያስፈልግበት አንዱ ምክንያት የመጽሐፉ ውስብስብ ነገረ-መለኮታዊ ትንታኔ የጸሐፊውን ዓላማ ሰው በቀላሉ ሊረዳው እንዳይችል ስላደረገበት ነው፡፡ ለአንባቢዎቹ ስለ ነገረ-መለኮታዊ አስተምህሮዎች መረጃ ሊያቀብላቸው ብቻ አልፈለገም፡፡ አስተምህሮአዊ መረጃን የሚያቀርብላቸው የተለያዩ አስተሳሰቦችንና ድርጊቶችን የራሳቸው እንዲያደርጉ ለመምከር ነው፡፡ መጽሐፉን “የምክር ቃል” ብሎ ሲጠራም ማለት የፈለገው ይህንኑ ነው፡፡ ይህንን አጣዳፊነት ልብ ካላልን፣ የዕብራውያንን መጽሐፍ ወሳኝ ኢድማስ እንስተዋለን፡፡

የጸሐፊው የምክር ቃል ጥብቅነት ለተደራሲያኑ ባቀረበው ምክር ድግግሞሽ ውስጥ እንዴት እንደተንጸባረቀ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ ጸሐፊው የተከተለው አሳማኝ ቅርፅ ተደራሲያኑን ለመምከር ያለውን ጉጉት እንደሚገልፅም እንመልከት፡፡

## አሳማኝ ቅርፅ

የዕብራውያን መጽሐፍ በጣም አሳማኝ በመሆኑ ተለይቶ ይታወቃል፡፡ ይህንም ስንል በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተሳካላቸው ተናጋሪዎች ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ስነ-ጽሑፋዊ አቀራረቦችን አሳማኝና አጣዳፊ ሙግት በሚያቀርብ መንገድ ይዟል ማለታችን ነው፡፡ እነዚህ የማሳመኛ ቅርፆች በሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አሁንም አሁንም ይታያሉ፣ በዕብራውያን ውስጥ ግን ይበልጥ በተደጋጋሚ ይገኛሉ፡፡

> *በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጠንካራ ስነ-ጽሑፋዊና የማሳመን ብቃት ያለው ጸሐፊ እንደፃፈው ምሳሌ የሚሆንልን የዕብራውያን መጽሐፍ ነው፣ እነዚህ ክህሎቶች የጸሐፊውን ዓላማ ለማሳካት በእጅጉ ያግዛሉ፡፡ የክርስቶስን የበላይነት እና አዲሱ ኪዳን ከአሮጌው የሚበልጥ መሆኑኑን ሊያሳየን ይሞክራል፣ ይህንንም የሚያደርገው እጅግ አሳማኝ በሆነ ስነ-ጽሑፋዊ*

*ሙግት ነው፡፡ ግቡንም ለማሳካት በርካታ የተለያዩ አወቃቀሮችን ይጠቀማል፡፡ እጅግ ውብ በሆነ መንገድ በማዋቀር፣ አሳማኝ ንግግሮችን በመጠቀም ተደራሲያኑን በመማረክ ከዚያም ደግሞ በሚያቀርበው ሙግት ሊያሳምናቸው ይጥራል፡፡ (ዶ/ር ማርክ ኤል. ስትራውስ)*

አንደኛው ማሳመኛ፣ በግሪክኛው *synkrisis* ይባላል፡፡ ይህም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ግልፅ ማነፃፀሪያ በማቅረብ ተደራሲያኑን ከተናጋሪው አመለካከት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ የተቀረፀ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ *synkrisis* የሚለው ቃል በዕብራውያን 7፡11-28 ውስጥ ይታያል፡፡ በዚያ ውስጥ ኢየሱስ በዘፍጥረት መጽሐፍ ካህናዊ ንጉሥ ሆኖ እንደተጠቀሰው እንደ መልከጼዴቅ ካህናዊ ንጉሥ ነው ብሎ ይሟገታል፡፡ ጸሐፊው የራሱን የእምነት አቋም ለማረጋገጥ ከመሞከር ይልቅ፣ በክርስቶስና በመልከጼዴቅ መካከል ያሉትን ስምንት ማራኪ ንፅፅሮች ለተደራሲያኑ ያቀርባል፡፡ በዚያም፣ ወላጆቻቸውን፣ ዘራቸውን፣ ልደታቸውን፣ ቢሮአቸውን፣ ተግባሮቻቸውን፣ ማእረጋቸውን እና ድሎቻቸውን ጠቅሷል፡፡ እነዚህ ዝርዝር ንፅፅሮች ኢየሱስ ታላቁ የንጉሥ ካህን ነው ከሚለው አንፃር ያለውን ብዥታ ለማስወገድ በዓላማ የተቀረፁ ናቸው፡፡

በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ሌላው አሳማኝ ንግግር *exempla* የተሰኘው ነው፡፡ *Exempla* አንድን አመለካከት ሰዎች አምነው እንዲቀበሉት ለማድረግ በሚቀርብ ሙግት ውስጥ በቅደም ተከተል የሚደረደሩ መግለጫዎች ወይም ምሳሌዎች ዝርዝር ነው፡፡ ይህ የአነጋገር ስልት ታዋቂ በሆነውና ጌታን በመታመን የጸኑቱ በተዘረዘሩበት በዕብራውያን 11 ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚያም ጸሐው፣ አቤልን፣ ሔኖክን፣ ኖህን፣ አብርሃምን፣ ሳራን፣ ያዕቆብን፣ ዮሴፍን፣ ሙሴን፣ እስራኤላውያንን፣ ረዓብን፣ ጌዲዮንን፣ ባርቅን፣ ሳምሶንን፣ ዮፍታሔን፣ ዳዊትን፣ ሳሙኤልን እና ነቢያትን በስም ይጠቅሳል፡፡ ይህ ረጅም ዝርዝር የተዘጋጀበት ዓላማ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሚያልፉበት ስደትና መከራ ውስጥ በታማኝነት መጽናት እንደሚገባቸው ተደራሲያኑን ለማሳመን ነው፡፡

በዕብራውያን ጸሐፊ ጥቅም ላይ የዋለው ሦስተኛው አሳማኝ ስልት በዕብራይስጡ አገባብ *qol wahomer* የተሰኘው ነው፡፡ ይህ አገላለጥ በግሪኮ-ሮማዊውም ሆነ በራቢዎች ትውፊት ውስጥ የታወቀ ሲሆን ሲተረጎምም “ከቀላል ወደ ከባድ”፣ “ከትንሽ ወደ ትልቅ”፣ “ከቀላል ወደ ውስብስብ” ሊባል ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሙግት አብዛኛውን ጊዜ ቀላልና ተደራሲያኑ ክርክር ከማያነሱበት ነገር ይነሳል፡፡ ከዚያ ግን ይበልጥ ወደተወሳሰበ ማጠቃለያ ያድጋል ማለትም ተደራሲያኑ በመጀመሪያ በጥርጣሬ ይመለከቱት የነበረውን ነገር አሁን በቀላሉ ይቀበሉታል፡፡ በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ ይህ መከራከሪያ የሚናገረው፣ ቀላሉ መነሻ እውነት ከሆነ፣ አስቸጋሪው ድምዳሜም እውነት ሊሆን ግድ ነው የሚለውን ነው፡፡ ይህ አሳማኝ ንግግር በዕብራውያን 10፡28-29 የተቀመጠበትን መንገድ አድምጡ፡

***የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? (ዕብ 10፡28-29)***

በዚህ ስፍራ ጸሐፊው ተደራሲያኑ ከሚረዱት መነሻ ይጀምራል፡፡ ያም የሙሴን ህግ የናቀ ሰው የሚጠብቀው የሞት ቅጣት መሆኑ ነው፡፡ ከዚያም ጫን በማለት፣ ከሙሴ የሚበልጠውን “የእግዚአብሔርን ልጅ” “የረገጠ” “እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?” በማለት ተደራሲያኑን ይሞግታል፡፡

እነዚህ ምሳሌዎች የጸሐፊው ዓላማ ምን ያህል አጣዳፊነት እንዳለው እንድንመለከት ያግዙናል፡፡ ተደራሲያኑ እጅግ ከባድ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ያውቃል ስለዚህም እጅግ አስቸጋሪ ውሳኔ የሚወስኑበት ጊዜው አሁን እንደሆነ ተረድቷል፡፡ ስለዚህ በተቻለው አቅም ሁሉ ትክክለኛውን ውሳኔ እንዲወስኑ ይመክራቸዋል ያሳስባቸዋልም፡፡

እንግዲህ የጸሐፊው ዓላማ በምክሮቹ ጥብቅነት ምን ያህል እንደተጠናከረ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ መጽሐፉ ሁለተኛ ገፅታ መሸጋገር ይገባናል፣ ያም የእነዚህ ምክሮች ግብ ነው፡፡

# የምክሩ ቃል ግብ

የዕብራውያን መጽሐፍ ገዢ ዓላማ በዚህ መንገድ ሊገለፅ እንደሚችል ቀደም ብለን አይተናል፡

> ***የዕብራውያን ጸሐፊ የጻፈው ተደራሲያኑ በአካባቢያቸው የተስፋፋውን የአይሁድ አስተምህሮ በመቃወም ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ለመምከር ነው፡፡***

ይህ ፍቺ እንደሚያረጋግጥልን፣ የጸሐፊው የምክር ቃል ግብ መንታ ነው፡፡ ተደራሲያኑ በአካባቢያቸው ያለውን የአይሁድ አስተምህሮ እንዲቃወሙ ደግሞም ለመሲሁ ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ይፈልጋል፡፡ ጸሐፊው በአካባቢው ያለውን የአይሁድ አስተምህሮ እንዲቃወሙ ተደራሲያኑን እንዴት እንዳሳሰበ በመጀመሪያ እንመልከት፡፡

## በአካባቢው ያለውን አስተምህሮ መቃወም

የዕብራውያን መጽሐፍ ተደራሲያን በመከራና በስደት ውስጥ እያለፉ መሆኑንና ይህም ስደትና መከራ ወደ ክህደት እንዲሄዱ እየፈተናቸው መሆኑን ጠቅሰናል፡፡ ይህ ፈተና ግን ጅማሬው ላይ ጨርሶ የማንገምተው ነው፡፡ የሚመስለውም ዕብራውያን በተጻፈበት ወቅት፣ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ መለያዎቻቸው የሆኑትን የእምነት አቋሞች ቸል በማለት በአካባቢያቸው ካለው የአይሁድ ማኅበረሰብ ጋር በጥብቅ ካስማሙ ከስደት ስጋት ያርፋሉ፡፡

በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት፣ አይሁድ ልዩ ታክስ ይከፍሉ፣ በየዘመናቱም ስደትና መከራ ይደርስባቸው ነበር፡፡ በሮሜ አገዛዝ ስር የነበሩ የአይሁድ ማኅበረሰብ ግን እምነታቸውን ማራመድ ይችሉ ነበር፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት፣ ነገሩ ለክርስቲያኖችም እንደዚያው ነበር ምክንቱም ክርስቲያኖቹ ከይሁዲነት ጋር ተዛማጅነት እንዳላቸው ይቆጠሩ ነበር፡፡ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ግን፣ ክርስቲያኖች እንደ አንድ የአይሁድ የእምነት ጎራ መታየታቸው እየደበዘዘ መጣ፡፡ እንዲያውም፣ የሐዋርያት ሥራ እንደሚዝብልን በጳውሎስ ዘመን፣ የአይሁድ ምኩራቦች የክርስቶስን ተከታዮች ይቃወሙ የአካባቢው ባለሥልጣናትም እንዲያንገላቷቸው ያነሳሱ ነበር፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ የዕብራውያን ቀደምት ተደራሲያንም ይገጥማቸው የነበረው ተመሳሳዩ ሁኔታ ነው፡፡ ይህም የረጅም ዘመን መከራቸው ከክርስትና እምነት ተቃራኒ የነበረውን የአይሁድን ማኅበረሰብ አስተምህሮ እንዲቀበሉ እየተፈታተናቸው ነበር፡፡

የሚያስገርመው፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ከአይሁድ ግብዝነትና ሕገኝነት ጋር በቀላሉ የሚዛመዱ ነገሮችን ጉዳዮች አልዳሰሰም፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በጣም ወሳኝ የመሆናቸውን ያህል፣ በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ዐቢይ ስፍራ አልተሰጣቸውም፡፡ ይልቁኑ፣ ጸሐፊው በተቀዳሚነት ያነሳው የተሳሳቱ እምነቶችን፣ በተለይም ከፓለስታይን ይሁዲነት ዋና መስመር ወጣ ብለው በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ እየጎለበቱ የነበሩትን ነው፡፡

***ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና። (ዕብ 13፡9)***

በዚህ ጥቅስ፣ ጸሐፊው "በጸጋ መጽናትን" "በሃይማኖታዊ መብሎች" ከመጽናት ጋር ያነፃፅራል፡፡ ይህ ውሱን ትኩረት የተለመደ ነው፡፡ ግን ይህ ነገር "እንግዳ ትምህርቶች" ተብለው ከተጠቀሱት አንዱ መሆኑንም ልብ ማለት ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ያልተለመዱ ወይም እንግዳ ትምህርቶች በአካባቢው የአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ እየተሰጡ ነበር ማለት ነው፡፡ እንግዲያው፣ ተደራሲያኑ ሊከተሏቸው እየተፈተኑባቸው ያሉት "እንግዳ ትምህርቶች" ምንድን ነበሩ?

ባለፈው ምዕተ-ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ፣ በቁምራን ከተገኘው የሙት ባህር ጥቅልል የተነሳ በዚህ ጥያቄ ረገድ ይነሱ የነበሩ በርካታ ጠቃሚ ግንዛቤዎች ፍንትው ብለው ወጡ፡፡ ይህ ረጅም ዘመናት ጠፍቶ የነበረ የዶሴዎች ስብስብ የብሉይ ኪዳንን ምንባቦችን፣ በተጨማሪ ደግሞ በሙት ባህር አቅራቢያ ተበታትነው የነበሩ የአይሁድ ማኅበረሰቦች መለያዎች የነበሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ ጽሑፎችንም ያካተቱ ነበሩ፡፡ *The Rule of the Community*, *The Damascus Covenant*, the *War Scroll*, *The Midrash on Melchizedek*, የመጀመሪያውን *1 Enoch* called "The Book of the Watchers" እና "The Book of Dreams" የተሰኙ መጽሐፍትንም የያዘ ነበር፡፡ እነዚህ መጻሕፍት በዕብራውያን መጽሐፍ ከተዳሰሱ ነገረ-መለኮታዊ አስተምህሮዎች ጋር በቅርብ ተዳዳኝነት ያላቸውን በርካታ ትምህርቶች ይዘው ነበር፡፡

እንግዲህ፣ እነዚህ አስተምህሮዎች ለዚህ ማኅበረሰብ የብቻው የነበሩ እንዳልነበሩ ማስታወስ ይገባል፡፡ በሜዲትራኒያን አካባቢ የነበሩ የአይሁድ ቡድኖችም ተመሳሳይ አመለካከት ነበራቸው፡፡ እንዲያውም፣ የኤፌሶን እና የቆላስይስ መጻሕፍት በየአካባቢያቸው ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ፡፡ ሆኖም በቁምራን የተገኙት መጻሕፍት በዕብራውያን ከተነሱት ጉዳዮች ጋር ለሚመሳሰሉ ርዕሰ ጉዳዮች የሰጡትን ትኩረት ልብ ስንል የዕብራውያን መጽሐፍ ስለ አይሁድ እምነቶች የሰነዘረውን ምክር ይበልጥ እንድንረዳ ያስችለናል፡፡

> **የሙት ባህር ጥቅልሎች ከተገኙት ሁሉ እጅግ አስደናቂ መዛግብት ናቸው፡፡ መዛግብቱ፣ በቁምራን በረሃ ይኖሩ የነበሩ አክራሪ የአይሁድ ወገኖች ሥራዎች ሲሆኑ ራሳቸውንም ከአይሁድ የላቁና አይሁድ አይነኬ ከሚሉት በተለይም ከመቅደሱ ውስብስብ ጉዳዮች ተፃራሪ እንደሆኑ ከሚገልጡት ወገን ናቸው፡፡ እናም፣ ከዕብራውያን መጽሐፍ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ፣ በቁምራን ያሉት ወገኖች ራሳቸውን የሚቆጥሩት በአዲስ ኪዳን አዲስ ቤተመቅደስ ከሚጠብቁት ወገን እንደሆኑ አድርገው ነው፡፡ በአሮጌው ኪዳን ውስጥ የነበሩት አንዳንድ ሃይማኖታዊ ወነች እንዳረጁና እንዳፈጁ እንዲዘልቁ ዝም ብሎ ከመተው ይልቅ የዕብራውያን ጸሐፊ እንደሚመክረው ይበልጥ ጠንካራ እንዲሆኑና እንዲታደሱ የቁምራን ቡድኖች በእውነት መሻቱ ነበራቸው፡፡** (ዶ/ር ሲዓን ማክዶን)

በዚህ ትምህርት፣ በዕብራውያን መጽሐፍና በቁምራን መዛግብት ውስጥ የተገኙትን አራት ርዕሶች በስሱ እንዳስሳለን፡፡

**የበዓላት ምግቦች፡፡** በመጀመሪያ ደረጃ፣ በዕብራውያን 13፡9 ውስጥ በበዓላት የሚቀርቡ ምግቦችን አስመልክቶ ጸሐፊው በተቃራኒው እንደተናገረ ጠቅሰናል፡፡

*ge*ተዘግቧል፡፡ ከሌሎች በርካታ ነገሮች በተጨማሪ፣ የቁምራን ማኅበረሰብ የተቀደሱ ምግቦችን በአንድነት ይመገባሉ እነዚያም በተለየ መንገድ ለዘንድ ነገር የተለዩ ምግቦች ናቸው፡፡

***መሠረታዊ አስተምህሮዎች፡፡*** በሁለተኛ ደረጃ፣ በዕብራውያን መጽሐፍ ከየዐይነቱ የቀረቡት መሠረታዊ ትምህርቶች በቁምራን ምንባቦችም ውስጥ ተገኝተዋል፡፡

ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 6፡1-2፣ ጸሐፊው፣ ንስሓን፣ እምነትን፣ የመንጻት ሙብትን (ወይም ጥምቀቶችን)፣ እጆችን መጫንን፣ የሙታንን ትንሣኤ እና የዘላለምን ፍርድ ጠቅሷል፡፡ እጅግ ማራኪ በሆነ መንገድ፣ *The Rule of the Community እና War Scroll* የተሰኙት የቁምራን ጽሑፎች በፓለስታይን ከነበረው የይሁዲነት ዋና አስተምህሮ በተለየ መንገድ ለእነዚህ ተመሳሳይ ጉዳዮች ትልቅ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡

***መላእክት፡፡*** በሦስተኛ ደረጃ፣ የቁምራን ስነ-ጽሑፍ በዕብራውያን መጽሐፍ ስለ መላእክት የተሰጠውን ትኩረት እንድንገነዘብ ያግዘናል፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ስለ መላእክት ያለውን እምነት በተለያዩ ምንባቦች ነካክቶታል፡፡ ይህ ትኩረት **The Rule of the Community, The Damascus Covenant, *እና the* War Scroll, *ደግሞም* 1 Enoch *"The Book of the Watchers" እና "The Book of Dreams."*** ተብለው በሚጠሩት መጻሕፍት ውስጥ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይነት ላላቸው አስተምህሮዎች ምላሽ ለመስጠት ነበር፡፡ እነዚህ መጻሕፍት የመልካምና የክፉ መላእክትን ኃይል፣ ለመለኮታዊ መገለጥ መልእክተኛ ስለመሆናቸውና አናሳ በሆኑ የሰው ዘሮች ላይ ስለሚኖራቸው ተፅዕኖ እያሞጋገሱ ይናገራሉ፡፡ ግልፅ በሆነ መንገድም፣ የዕብራውያን ተደራሲያንም ወደ እነዚህ አስተምህሮዎች መሳብ ጀምረው ነበር፡፡

***መልከጼዴቅ፡፡*** በአራተኛ ደረጃ፣ በቁምራን የተገኙት መዛግብት የዕብራውያን ጸሐፊ ባልተለመደ መንገድ በብሉይ ኪዳኑ መልከጼዴቅ ላይ የሰጠውን አጽንዖት እንድንረዳ ያግዙናል፡፡

የዕብራውያን ጸሐፊ መልከጼዴቅንና ኢየሱስን ለምን ማነጻጸር እንዳስፈለገው ማብራራት ረዘም ላለ ጊዜ የተርጓሚዎች ፈተና ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡ በተለይም በቁምራን የሚገኝ አንድ ምንባብ፣ ተደጋግሞ *11QMelchizedek ወይንም The Midrash on Melchizedek* በመባል የሚታወቀው ጽሑፍ መልከጼዴቅ በመጨረሻው ዘመን የስርየትን ቀን የሚያውጅና ለእግዚአብሔርም ህዝብ የፍፃሜውን ማስተሰረያ የሚያደርግ ሰማያዊ አምሳል ነው በማለት በስህተት ያስተምራል፡፡ ከሁሉም ገፅታዎች ይልቅ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ተደራሲያን በእዚህና በተመሳሳዮቹ የእምነት አቋሞች በእጅጉ ተፈትነው ነበር፡፡

በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ ተሰራጭተው የነበሩትን የስህተት አስተምህሮዎች ዓይነት መለየታችን የዕብራውያን ጸሐፊ ተደራሲያኑ እነዚህን የስህተት አስተምህሮዎች በመቋቋም ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ለምን እንደፈለገ እንድንረዳ ያስችለናል፡፡

> **በዕብራውያን መጽሐፍ አስተምህሮና እና በሙት ባህር ጥቅልሎች አስተምህሮ መካከል ማራኪ የሆኑ በርካታ ጉድኝቶች አሉ፡፡ ከሉም ወሳኝ የሆነው ደግሞ ሁለቱም እግዚአብሔር ለህዝቡ ያዘጋጀው የፍፃሜ ድነት ሊከናወን ጫፍ በደረሰበት የመጨረሻ ዘመን ውስጥ የሚኖሩ ስለመሆናቸው ያላቸው ጽኑ እምነት ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ በዕብራውያን የእግዚአብሔር ድነት መጥቷል ተብሎ የተጠቀሰ ሲሆን፣ በሙት ባህር ጥቅልሎች ግን በየትኛውም ጊዜ ይከናወናል ብለው መጠበቃቸው ይለያቸዋል፡፡ ከሁሉ ማራኪ የሆነው ንፅፅር ግን ስለ መልከጼዴቅ ሃላፊነት የጠቀሱት ነው፡፡ በዕብራውያን መጽሐፍ የተጠቀሰው መልከጼዴቅ፣ በዕብራውያኑ ጸሐፊ የተጠቀሰው የኢየሱስ ሊቀካህንነት እንደ አሮን ሥርዓት ደግሞም እንደ አሮጌው ኪዳን የሆነ ሳይሆን እንደመልከጼዴቅ ሥርዓት ነው የሚለውን ነገረ-መለኮት ለማጉላት ነው ምክንያቱም መልከጼዴቅ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ አብርሃምን የተገናኘ ህጋዊ ሊቀ ካህን ሆኖ እናየዋለን፡፡ እናም ስለዚህ፣ በንፅፅር የቀረበው ይህ መልከጼዴቅ ነው፡፡ መልካም፣ ከሙት ባህር ጥቅልሎች ውስጥ፣ በሙት ባህር ጥቅልሎች በ11ኛው ዋሻ ውስጥ ከመገኘቱ የተነሳ 11QMelchizedek በመባል የሚታወቅ ጥቅልል አለ፡፡ ያም መልከጼዴቅን እንደ ኃያል ሰማያዊና ባለ ግርማ መሲህ፣ ድነትን እንደሚያስገኝ መሲህ ይገልፀዋል፡፡ ስለዚህ፣ መልከጼዴቅ በዕብራውያን**

**መጽሐፍ ውስጥ የክርስቶስ ተምሳሊት ሆኖ የተገለጠ ሲሆን፣ በሙት ባህር ጥቅልል መሲሃዊ ንጉሥ እንደሚሆን ተገልጧል፡፡ ስለዚህም በዕብራውያን በተጠቀሰው መልከፄዴቅና በሙት ባህር ጥቅልል በተገለጠው መልከፄዴው መካከል ያለው ግንኙነት ለምሁራኑ እንቆቅልሽ ሆኗል፡፡ አስደናቂ ንፅፅር ነው፡፡ (ዶ/ር ምርክ ስትራውስ)**

የዕብራውያን መጽሐፍ የምክር ቃል ግቡ ተደራሲያኑ በአካባቢያቸው ያለውን የአይሁድ አስተምህሮ እንዲቃወሙ ማሳሰብ ብቻ አልነበረም፡፡ ከዚያ አልፈው፣ ለመሲሁ ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁም ይፈልጋል፡፡

## ለኢየሱስ ታማኝ ሆኖ መዝለቅ

የዕብራውያን ጸሐፊ ተደራሲያኑ ለኢየሱስ የታመነ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያቀርብላቸውን ጥሪ ከግቡ ለማድረስ የምክሩን ቃል በአምስት ዐቢይ ክፍሎች ያቀናብራል፡፡ በሚቀጥለው ትምህርታችን እነዚህን ክፍልፋዮች በበለጠ ጥልቀት እንመለከታቸዋለን፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ግን በእያንዳንዳቸው ውስጥ በሚገኘው ማዕከላዊ ጉዳይ ላይ ማትኮር ይጠቅማል፡፡

በዕብራውያን 1፡1-2፡18፣ ከመላእክት መገለጥ ይልቅ ክርስቶስ የሚልቅ መሆኑን ተደራሲያኑ እንዲያረጋግጡለት የዕብራውያን ጸሐፊ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

የዕብራውያን መጽሐፍ ስለ መላእክት የተሳሳቱ እምነቶችን እንደሚፋለም ቀደም ብለን ጠቅሰናል፡፡ በርካታ የአይሁድ ጽሁፎች መላእክትን እንደ ኃያል፣ ክቡር ፍጥረታትና ለሰው ልጆችም መለኮታዊ መገለጥን እንደሚያመጡ አድርገው ያከብሯቸዋል፡፡ ይህ ለመላእክት የሚሰጥ ክብር ለክርስቶስ ተከታዮች ብርቱ ፈተና ነበር፡፡ ኢየሱስ ስጋና ደም ነበር፡፡ ታድያ አንድ ሰው ከመላእክት መገለጥ ይልቅ እርሱ የተናገረውን እንዴት ሊከተል ይችላል? የዕብራውያን ጸሐፊ ለዚህ የአይሁድ አስተምህሮ ምላሽ የሚሰጠው ከብሉይ ኪዳን፣ ከኢየሱስ ሕይወት፣ ከሞቱ፣ ከትንሣኤው፣ ከእርገቱ እና በክብር ከመመለሱ በመጥቀስ እርሱ ከመላእክት እጅግ እንደሚበልጥ በማሳየት ነው፡፡

ሁለተኛው የዕብራውያን መጽሐፍ አንጓ፣ በ3፡1-4፡13 የሚገኘው ሲሆን፣ ኢየሱስ ከሙሴ ሥልጣን እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡

ኢየሱስን የሚከተል የትኛውም ሰው እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት የሰጠውን የመስዋዕት ሥርዓት እንደማይጠብቅ ግልፅ ነው፡፡ የአይሁድ ማኅበረሰብ ደግሞ ክርስቲያኖች ወደ ሙሴና ወደ መንገዶቹ እንዲመለሱ ያባብሏቸዋል፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊም ሙሴ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ እንደነበር ያረጋግጣል፡፡ ኢየሱስ ግን ከእርሱም ይበልጣል ምክንያቱም እርሱ አንድያ ልጁ ነውና፡፡

የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ መላእክትና ስለ ሙሴ ከተናገረ በኋላ፣ በ4፡14-7፡28 ወደሚኘው የመልከፄዴቅ ክህነት ይሸጋገራል፡፡

በዚህ ክፍል፣ ኢየሱስ እንደ መልከፄዴቅ ሥርዓት የንጉሥ ካህን ነው ሲል ጸሐፊው ሙግቱን ያቀርባል፡፡ የአይሁድ ማኅበረሰብ ግን መልከፄዴቅ በመጨረሻው ዘመን የሚገለጥ ታላቅ የንጉሥ ሊቀ ካህን ነው ብለው ከማመናቸው የተነሳ ተደራሲያኑ የኢየሱስን መሲህነት እንዳይቀበሉ በግልፅ

ያስተምራሉ፡፡  ለዚህ ምላሽ ይሆን ዘንድ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ለኃጢአት ሥርየትን ያስገኝ ዘንድ የሚገለጥ የንጉሥ ካህን ነው በማለት ይገልጣል፡፡

በ8፡1-11፡40 ውስጥ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ በኢየሱስ የተገለጠው አዲስ ኪዳን ከሁሉ እንደሚበልጥ ያብራራል፡፡

ኢየሱስ በኤርምያስ የተነገረውን አዲስ ኪዳን ያመጣ  መካከለኛ ነው ብለው ክርስቲያኖች የሚያቀርቡትን ማስረጃ የአይሁድ ማኅበረሰብ አስተምህሮ እንዲጠራጠሩት ያደርጋል፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ ግን ኢየሱስ በእርግጥ የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በመጨሻው ዐቢይ ክፍል፣ በ12፡1-13፡25 ውስጥ፣ ተደራሲያኑ ጽናትን በተግባር እንዲለማመዱ የዕብራውያን መጽሐፍ በበርካታ መንገዶች ማብራሪያ ያቀርባል፡፡

ይህ ክፍል ረጃጅም የምክር ቃሎችን ደግሞም ማብራሪያቸውን አከታትሎ ያቀርባል፣ በአካባቢያቸው እና በሌላም ስፍራ ከሚገኙ የአይሁድ ማኅበረሰብ በእምነታቸው ምክንያት ስለሚገጥማቸው ተግዳሮት በማንሳት፣ ተደራሲያኑን ለማበረታታትና መንፈሳቸውን ለማንቃት ይፅፋል፡፡ በኢየሱስ አማካይነት እግዚአብሔር የሰጣቸውን በረከቶች በማሳሰብ ለመሲሁ ለኢየሱስ የታመነ አገልግሎት በመስጠት እንዲፀኑ ይመክራቸዋል፡፡

> **የዕብራውያን ጸሐፊ፣ በበርካታ የምክር ቃሎቹ፣ አዎንታዊ በሆነ መልኩ፣ አንባቢዎቹ በጽናት እንዲቆሙ ያበረታታቸዋል፡፡ አንዳንድ ቋንቋዎቹ በጣም ጨዋነት የሞላባቸው፣ ተለማማጭ እና የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ግን፣ እውነቱን ለመናገር፣ በጣም የሚያስፈራሩ ናቸው፡፡ የሚጀምረውም ገና በምዕራፍ 2 ነው፡፡ “የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ከወደቁ፣ እኛማ አዲሱን ኪዳን የተቀበልን፣ ጌታ ኢየሱስን ያወቅን፣ ለእኛ የተሰጠውን ታላቅ መዳን ቸል ብንል ምንኛ እጅግ ይከብድብን ይሆን?” በማለት ሙግቱን “ያ እንዲህ ከሆነ፣ ይህኛውማ እንዴት ይልቅ?” በሚል ዘይቤ በመጽሐፉ ውስጥ ደጋግሞ በማሳየት ያቀርበዋል፡፡ ከዚያም በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ የክህደት ምንባባት ተብለው የሚታወቁትን በምዕራፍ 6 እና 10 የሚገኙትን ክፍሎች በክርስቶስ ጠንካራ እምነት አለን የሚሉትን በግልፅም ለተወሰነ ጊዜ የተከተሉትን እና ኋላ የተንሸራተቱትን ለማስጠንቀቅ ይጽፋል፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ በዕብራውያን ምዕራፍ 3 የብሉይ ኪዳንን ትረካ ካቀረበ በኋላ፣ ከግብፅ ባርነት ወጥተው ባለመጽናታቸው ምክንያት ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሳይገቡ እንደቀሩት እንደ ብሉይ ኪዳኖቹ ቅዱሳን አትሁኑ በማለት ጸሐፊው ያሳስባል፡፡ እነርሱ በምድረ በዳ ወድቀው ቀሩ፡፡ ከጥቂቶች በቀር፣ ትውልዱ በጠቅላላ ተወገደ፡፡ እንግዲህ የማበረታቻ ምጋቤዎቹ ይህንን ጉድኝት የሚያሳዩ ነበሩ እንጂ ባዶ እሹሩሩ የተሞሉ አልነበሩም፡፡ ይልቁኑ እጅግ የጋሉና የክርስቶስን ክብር በማጉላት ወደ እርሱ የሚስብባቸው ነበሩ፡፡ ደግሞም ነገሩ የዋዛ እንዳልሆነና ብርቱ ትግል የሚጠይቅ ፈታኝ ጉዳይ ስለሆነ ዙሪያ ዙሪያውን በመሸከርከር መቀለድ እንደማይገባም እቅጩን ይናገራል፡፡ (ዶ/ር ዲ.ኤ. ካርሰን)**

# ማጠቃለያ

በዕብራውያን ዳራና ዓላማ ላይ በተነጋገርንበት በዚህ ትምህርት፣ የዕብራውያንን መጽሐፍ ዳራ ማለትም ጸሐፊውን፣ ተደራሲያኑን እና የተጠናቀረበትን ወቅት አካትተን ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም ተደራሲያኑ በአካባቢያቸው ከተስፋፋውን የአይሁድ አስተምህሮ በመመለስ ለመሲሁ ለኢየሱስ የታመነ አገልግሎት መስጠታቸውን እንደገና እንዲቀጥሉ እንዴት እንደመከራቸው በመመርመር በዕብራውያን መጽሐፍ ዓላማ ላይ አትኩረናል፡፡

የዕብራውያን መጽሐፍ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ይልቅ እጅግ ሞጋች መጽሐፍ ነው፡፡ እርሱ ከሚያስተምራቸው ነገሮች መካከል ጥቂቱን ብቻ ለመግለጥ ከመሞከር በዘለለ ምንም ልናደርግ በማንችልበት መጠን እጅግ በርካታ ነገር ተሸክሟል፡፡ ሆኖም፣ ከእነዚህ ውስብስብ ትምህርቶች ልንጠቀም የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ እንደ ዘመኑ የክርስቶስ ተከታዮች፣ ለኢየሱስ ያለንን መሰጠት በማመቻመች ራሳችንን ከሕይወት ፈተና ለማስመለጥ እንፈተናለን፡፡ ሆኖም የዕብራውያን ጸሐፊ ቀደምት ተደራሲያኑን እንዴት አጣዳፊ ምክር እንደለገሳቸው ለማድመጥ ልባችንን ከከፈትን፣ የቱንም ያህል ፈተና ቢገጥመን፣ በእምነታችን በርትነት በጽናት መቆም ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ማየት እንችላለን፡፡